ግድል ፣ በቃል ኪዳን ማስማር እና መካናትን በመሳለም የሚገኝ በረከት በ ምሥራቃውያን(Oriental)አብያተ ክርስቲያናት



እስከ ሺህ ትውልድ ምሕረት?
ገዳማትን በመሳለም መዳን?
ለብዙ ዓመታት በአንድ ቦታ ቆሞ መጸለይ?
የመካከለኛው ዘመን ግነት?

ሚያዝያ 2017
አዲስ አበባ

በናታን ጉታ
ሰኔ 2017



በሃይማኖት ላለ ሩጫ ጀማሪው ክርስቶስ ነው። የክርስቶስ የሆኑ ቅዱሳን በዓለም ያላቸው ኑሮ ልክ እንደ ክርስቶስ በመከራ የተሞላ ነው። ሕይወታቸው በሥጋዊ ቀመር የተኖረ ሳይሆን በአምላካዊ ድንቆች የታጀበ ነውና ለአዕምሮ የሚደንቁ ሁነቶች በተጻፉ ገድሎቻቸው ውስጥ እና በትውፊት በሚነገርላቸው ሕይወታቸው ውስጥ ሊገኝ ይችላል።

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅዱሣኑ የተጋድሎ ዜና [contention] በተጻፈባቸው የገድል መጻሕፍቶች ላይ ከሰሞኑን በ ፫ ንዑስ ክፍል ተለፋፍለው መቅረብ የሚችሉ ትችቶች ተነስተዋል።

፩ ለማመን የሚከብዱ "የተጋነኑ" የሚመስሉ የተጋድሎ ጽሑፎች ላይ...

፪ "እስከ ሺህ ትውልድ እምርልሃለው" የሚሉ እና ሌሎችም ለትውልድ የሚሆኑ ቃልኪዳኖች ላይ

፫ መካናትን በመሳለም የሚገኝ በረከት ላይ

ከላይ በተነሱት ጉዳዮች ላይ ለሚቀርበው ትችት እንደ ጥሩ ማዳመቂያ ሆኖ የቀረበው "ነገሩ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ብቻ የሚገኝ ነው" የሚል የሐሰት ክስ ነው። በመሆኑም የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በየ ርዕሰ ጉዳዩ ላይ ከጥቂት ምላሽ ጋር በሌሎች **oriental** አብያተ ክርስቲያናት ገድላት ውስጥ ያሉትን ተመሳሳይ አገላለጾች ማሳየት ነው። በዚኽም "በመካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ የተጨመሩ" የሚለውን የሐሰት ክስ ማፈራረስ ይቻላል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ያለውን ገድል ለማመሳከሪያነት የተጠቀምኩት "በኢትዮጵያ ብቻ በመካከለኛው ዘመን የተጨመረ" የሚለውን ውሸት ለማሳየት ብቻ እንጂ ለያዝነው ትውፊት ከሶሪያ እና ከግብጽ የልክነት ማረጋገጫ ስለሚያስፈልገን አይደለም።

በመሰረቱ ቤተክርስቲያን አንዲት ናት። በአንዲቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ **horizontally** የሚቀመጡ መናብርት አከባቢያዊ ትውፊት ይኖራቸዋል። በነዚህ መናብርት መካከል የበላይነት እና የበታችነት የለም።

አንዱ መንበር የኔ ብሎ የያዘውን አከባቢያዊ ትውፊት ልክነት ለማስረገጥ ከሌላ አቻው መንበር ማረጋገጫ ለማምጣት አይገደድም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ **EOTC** የያዘቻቸውን አከባቢያዊ ትውፊቶች ልክነት ከሌሎች መናብርት ትውፊት አንጻር ለመመዘን የሚሞክሩ ሰዎችን ሚዲያው ላይ ታዝበናል። ይኽ አይነቱ አካኼድ የጌታን ቤተክርስቲያን እንደ ኮንፌዴሬሽን የመመልከት ውጤት ነው።

የቅዱሳን ሁሉ በረከታቸው በቃልኪዳናቸው ከምንታመን ከኛ ጋር ይሁን አሜን።

በናታን ጉታ



፩ በገድለ ተክለ ሃይማኖት ላይ ቅዱሱ ከ፬ዐ ዓመት በላይ በአንድ ቦታ ቆሞ እንደ ጸለየ ተጽፏል ይኽና መሰል ተዓምራት ተዓማኒ ናቸው? በአኃት አብያተ ክርስቲያናት ለምን እንደዚህ አይነት የተጋነነ ተዓምር አይኖርም?

ቅዱሳን የክርስቶስን ሕይወት በምድርም በሰማይም የሚኖሩ ናቸው። በምድር የክርስቶስን መከራ ተቀብለው በሰማይ ደግሞ የክርስቶስ በሆነ ክብር ይከብራሉ። በመሆኑም በቅዱሳኑ የሚሰራ የትኛውም ድንቅ ሥራ ቢኖር እግዚአብሔርን እንድናከብት ምክንያት የሚሆነን ነው።

በተፈጥሮ ሕጎች ላይ ሁሉ ሃይል ያለውን ጌታ አመልካለው የሚል ክርስቲያን በገድላት ላይ ለተዘገቡ ታሪኮች ከተፈጥሮ ሕግ አንጻር ጥያቄ ሊያነሳ አይገባውም።

በአባታችን በቅዱስ ተክለሃይማኖት ገድል ላይ ተዘግቦ የሚገኘው "ለዓመታት በአንድ ቦታ መጸለይ" እንዴት ይብራራል? የሚለውን ጥያቄ በልባችን ይዘን ከዚህ ታሪክ ጋር paraller የሆኑ የአኃት አብያተ ክርስቲያናት ገድላትን እንፈልግ...

ኬልቄዶናውያን አብያተ ክርስቲያናትን ጨምሮ በምሥራቃዊው ንፍቀ ክበብ ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ "pillar saints -ባለ ምሶሶ ቅዱሳን" ተብለው የሚታወቁ ቅዱሳን አሉ። እነዚህ ቅዱሳን ይኽን ሥያሜ ያገኙት ለረጅም ጊዜ በአንድ ምሶሶ ላይ ቆመው በመጸለያቸው ነው። ይኸውም እንዲህ ያለው ልምምድ (ለረጅም ጊዜ በአንድ ቦታ መጸለይ) በገድለ ተክለ ሐይማኖት ብቻ ነገር ለማጋነን የገባ ሳይሆን በብዙ ቅዱሳን ገድላት ላይ የሚገኝ ድንቅ መሆኑን ያስገነዝበናል። ጥቂቶቹን እንመልከት...

Saint Simeon stylites The elder -ቅዱስ ስምዖን (ሶርያ ቤተክርስቲያን 5ኛ ክ/ዘ)

አሌፖ በምትባል አከባቢ 60 ጫማ ያኽል ከፍታ ባለው ምሶሶ ላይ ለ37 ዓመታት ያኽል ቀን እና ሌሊት እንደቆመ (እንደ ጸለየ) በገድሉ ተዘግቧል።



"st" Seraphim of Sarov (russian orthodox)

በሩሲያ ቤተክርስቲያን በቅድስና የሚታወቀው ይኽ አባት ለአንድ ሺህ ምሽቶች በአለት ላይ ሆኖ እንደ ጸለየ በገድሉ ተጽፎ እናገኛለን።

"st" Luke of Mt Stiron ("ቅዱስ" ሉቃስ የስቲሮን ተራራው)

ይኽ አባትም ለ20 ዓመታት ቀጥ ብሎ ቆሞ የጸለየ አባት ነው። በዚህም "the standing saint" በሚል ቅጽል እስከ መጠራት ደርሷል።

St Alypius the Stylite (ባዛንታይን 7ኛ ክ/ዘ)

pillar saint ተብለው ከሚታወቁት ቅዱሳን ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ለ 53 ዓመታት በ adrianople በምትገኝ ምሶሶ ላይ ቆሞ የጸለየ አባት ነው።

ከላይ ለአብነት ያነሳናቸው በአኃት እና በኬልቄዶናውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ ገድላት "ለብዙ ጊዜ በአንድ ቦታ ቆሞ መጸለይ" በኢትዮጵያ ብቻ ነገር ለማጋነን የገባ የፈጠራ ታሪክ ሳይሆን በብዙ ቅዱሳን የተፈጸመ ተጋድሎ መሆኑን የሚያሳየን ነው። በረከታቸው ይደርብን።

፪ መካናትን በመሳለም ሥርየተ ኃጢዓት ማግኘት።

በቤተክርስቲያናችን በምናነባቸው በብዙ ገድላት ውስጥ ለቅዱሳን ተሰጥተው ከምናገኛቸው የተለመዱ ቃልኪዳኖች ውስጥ "ቅጥርህን የተሳለመ ኃጢዓቱ ይቅር ይባላል" የሚሉ ናቸው። ለአብነትም ለግሸን ማርያም በሆነው ቃል ኪዳን ላይ ያለውን "ገዳሙን የተሳለመ ስርየተ ኃጢዓትን አግኝቶ እንደ አርባ ቀን ሕጻን ይሆናል" የሚለውን መመልከት ይቻላል።

እዚህ ጋር በመሳለም እና በመጎብኘት መካከል ያለውን መሰረታዊ ልዩነት ማወቅ ወሳኝ ነው። ሊጎበኝ በሚሄድ ቱሪስት እና ሊሳለም በሚሄድ አማኝ መካከል መሰረታዊ ልዩነት አለ። ሊሳለም የሚኼድ አማኝ ከፍ ባለ የልብ እምነት እና ጌታዬ ኃጢዓቴን ይቅር ይለኛል በሚል ጽኑዕ የልብ እምነት ከቤቱ የወጣ ነው። እንዲህ ላለው ጽኑ አማኝ የኃጢዓት ይቅርታ መሰጠቱ የጌታን መሃሪነት የሚያሳይ ነው።

እንዲህ ያለው አማኝ ከመካናት በረከትን ለማግኘት ሲጓዝ እንደ ጎብኚ አይቶ ብቻ የሚመለስ አይደለም። በቤተክርስቲያኑ የሚፈጸመውን ሰማያዊ ሥርዓት በእምነት የሚካፈል እንጂ። ይኽን ሰማያዊ ሥርዓት መካፈል ደግሞ የኃጢዓት ይቅርታን እንደሚያሰጥ የቤተክርስቲያን እምነቷ ነው።



በኛ ገድላት ላይ እንደሚገኙ ያሉ አገላለጾችን በሌሎች አኃት አብያተ ክርስቲያናት እና በኬልቄዶናውያን አብያተ ክርስቲያናት ገድላት ላይ ከሚገኙ Paraller ገለጻዎች ጋር እናስተያይ...

በግብጻውያን ትውፊት

St Menas wonderworker ቅዱስ ሚናስ ገባሬ መንክራት

በ6ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈውና የቅዱሱ ተዓምራት የተጻፉበት "the miracles of St Menas ቅዱስ ሚናስ ለአንዲት ሴት በራዕይ ተገልጦ የተናገራትን ነገር እንዲህ ያስነብበናል።

"Go and tell the people: Whoever comes to my sanctuary in faith whether near or far, whether rich or poor and calls upon my name, I will intercede for them before Christ. ሂጂና ለሕዝቡ ይኽንን ተናገሪ ወደ ቅጥሬ በእምነት ከሩቅም ከቅርብም የሚመጣውን እኔ ከክርስቶስ ዘንድ አማላጅ እሆነዋለው"

በሶርያውያን ትውፊት

st. Mar Behman እና st Sarah (ቅዱስ ማር ቤህማን እና ቅድስት ሳራ)

ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና በመመለሳቸው ምክንያት ሰማዕትነትን የተቀበሉት ሁለት የንጉስ ልጆች ከተገደሉ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ለመነኮሳቱ ተገልጦ ቃልኪዳንን እንዳበሰራቸው በ 6ኛው ክ/ዘ በተጻፈው The martyrdom of mar Benham ላይ እናገኛለን።

"From this day forward, all who come to this place whether for healing, for deliverance from demons, or to pray will receive mercy. Whoever lights a lamp here in faith, I will hear their prayer. And if they fast on the day of Behnam and Sarah's commemoration, their sins will be forgiven." ከዚህ ቀን ጀምሮ ወደዚህ ሥፍራ ለፈውስም ከአጋንንት እስራት ነጻ ለመሆን እንዲሁም ለጸሎት የሚመጣ ማንም ቢሆን ምሕረትን ይቀበላል። በእምነት በዚህ ሥፍታ መብራትን የሚያበራ ማንም ቢኖር እኔ ጸሎቱን እሰማዋለው። እንዲሁም በቤንሃም እና በሳራ መታሰቢያ እለት ጾምን ያደረገ የኃጢዓት ይቅርታን ያገኛል።"



በአርመን ትውፊት

st Gregory the illuminator

agathangelos በተሰኘው የአርመን ቤተክርስቲያን ታሪካዊ መጽሐፍ ላይ ደግሞ st gregory ከሞቱ አስቀድሞ የተሰጠውን ኪዳን እንዲህ ተናግሯል።

"let my body laid in thordan and know this the man who visit my grave with pure heart will recvieve blessing upon his household. his children will not stray from the faith"

የመቃብር ሥፍራዬን በንጹሕ ልብ ሆኖ የጎበኘ ሰው ለቤተሰቡ በረከትን ይቀበላል ልጆቹም ከሃይማኖት እንዳይወጡ በቃልኪዳኔ ይጠበቃሉ"

እነዚህ ሁሉ ከላይ ያነሳናቸው በአኃት አብያተ ክርስቲያናት ገድላት ውስጥ የሚገኙ ምንባባት ቅዱሳት መካናትን በመሳለም ሊገኝ ስለሚችል የኃጢዓት ይቅርታ በአንድነት የሚያስረዱ ናቸው። ስለዚህም በኢትዮጵያ ብቻ በመካከለኛው ዘመን የተጨመረ የሚለው ክስ ፍጹም ከእውነት የራቀ መሆኑን መረዳት እንችላለን።

፫ ልጆችን በቅዱሳን ስም በመሰየም በረከት ማግኘት

ሌላው ደግሞ ልጆችን በቅዱሳን ስም በመሰየም የሚገኝ በረከት ነው። ይኼም ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያነ አበው ጀምሮ የነበረ ትውፊት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ልጆችን በሰማዕታት ስም መሰየም የሰማዕታቱ የእምነት ጽናት እንዲጋባባቸው እንደሚያደርግ ተናግሯል።

፬ ለትውልድ የሚደረግ ምሕረት

ሌላው በቅዱሳን ቃልኪዳን ውስጥ መረር ያለ ተቃውሞ የሚደርስበት ክፍል በቃልኪዳናቸው ለትውልድ የሚደረገው ምሕረት ነው።



በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ደስ የሚላቸው ጻድቃን ለልጅ ልጅ የሚተርፍን ምሕረት ከእርሱ የሚያገኙ ስለመሆናቸው ራሱ እግዚአብሔር "እስከ ሺህ ትውልድ ምሕረትን የማደርግ"ዘጸ 20፥6 ብሎ ተናግሯል። ይኽ መሐሪነቱ በአዲስ ኪዳንም አልተቀየረም። እንደውም መገለጡ ከቀድሞ ይልቅ በዛ።

እግዚአብሔር ስለ ቅዱሳኑ የከፈተውን ይኽን የምሕረት በር ለመዝጋት መደፋፈር ከኛ ይራቅ! ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ባቀረበችው የምስጋና ጸሎት ውስጥ የሚገኘው "ምሕረቱም ለሚፈሩት ለልጅ ልጅ ነው።" የሚል ክፍልም ይኽንኑ ለልጅ ልጅ የሚተርፍ በረከት የሚያሳይ ነው።

እንዲህ ያለው ከአባት ወደ ልጅ የሚያልፍ በረከት እና ምሕረት ግን ልጅ እንዴትም ባለ ኃጢዓት ውስጥ ቢገኝ በአባቱ ጽድቅ የሚጸድቅበት አይደለም። ሕዝቅኤል 18፥11 "ጻድቅ አባቱ የሠራውን ሁሉ ባይሠራ ... በሕይወት አይኖርም፤ ይህን ርኩሰት ሁሉ አድርጎአልና ፈጽሞ ይሞታል፤ ደሙ በላዩ ላይ ይሆናል።" ተብሎ ተነግሯል። ስለዚህ በአባቶች ቃልኪዳን ለመባረክ የእውነትም የአባቶች ልጅ መሆን ይገባል።

በወንጌል ጌታችን "ቀዝቃዛ ውሃን በጻድቅ ስም ያጠጣ ዋጋው አይጠፋበትም" ብሎ ተናግሯል። ይኼ ማለት ግን ቀዝቃዛ ውሃ ማጠጣት ብቻ በክርስትና ያለን ሩጫ ይተካል ማለት አይደለም። በገድላት የሚገኙ ንባባትም ይኼኛው የወንጌል ክፍል በተተረጎመበት መንገድ የሚታዩ ናቸው።

በአኃት አብያተ ክርስቲያናት ገድላት ውስጥ የሚገኙ ተመሳሳይ ገለጻዎችን እንመልከት...

በሶርያ ትውፊት

ቅድስት ፌብሮኒያ ዘ ንጽቢ st. Febronia of Nisbis

በ6ኛው ክ/ዘ በተጻፈውና የቅድስቲቱ ገድል በተዘገበበት "ገድለ ቅድስት ፌብሮኒያ[acts of st. febronia] ላይ ቅድስቲቱ ወደ ግዞት ከመወሰዷ በፊት የጸለየችው ጸሎት እንዲህ ይነበባል ‘Lord, grant that whoever commemorates my martyrdom whether in their home or at my tomb will receive mercy for their children’s children. ጌታ ሆይ የሰማዕትነቴን መታሰቢያ በዓል በቤታቸው ወይም በመቃብር ሥፍራዬ የሚያደርጉ ለልጆቻቸው እና ለልጅ ልጆቻቸው የሚሆን ምሕረትን ይቀበሉ"



በግብጽ ትውፊት

ቅዱስ ጊዮርጊስ st George the martyr

Piermont morgan library ውስጥ በሚገኘው ገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ላይ ይኽ የቅዱስ ጊዮርጊስ ንግግር ተዘግቦ ይገኛል።

"Whoever builds an altar in my name or sheds tears for my martyrdom, I will claim their children's children for Paradise.ለስሜ መታሰቢያ የሚሆን መሰዊያን የሰራን ሰው ልጆቹን እና የልጅ ልጆቹን ለመንግስተ ሰማያት አበቃቸዋለው።"

st Mary of egypt ቅድስት ማርያም ግብጻዊት

በግብጽ ቤተክርስቲያን የ 14 baharamhat synaxarium ላይ ተዘግቦ የሚገኘው ቃልኪዳንም ከዚሁ ጋር ተያያዥ የሆነ ነገር ይገኝበታል።

"Mothers who confess their worst sins on my feast will walk into Paradise leading three generations by the hand.-በእለተ ቀኔ የከፋ ኃጢዓቷን የተናዘዘች እናት 3 ትውልዷቿን እየመራች ገነት ትገባለች"

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ በገድላት ላይ የሚገኙ ምንባባት የሚያሳዩን ከማሰብ የሚልቅ የጌታን ቸርነት ነው።

የቅዱሳን ሁሉ ጸሎታቸው በቃል ኪዳናቸው ከምንታመን ከኛ ጋር ይሁን አሜን